# እርዳታ ከላይ



አዘጋጅ፤ ዋትሰን ጉድማን

የማይሸጥ፡— በነፃ የሚታደል

## እርዳታ ከላይ

«እርዳታ ከላይ» በአርእስት ተዛማጅ የሆኑ ቅዱስ ጥቅሶችን ከልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማውጣጣት የተዘጋጀ ነው። በእኔ እምነት ከሁሉ የተሻለ የቅዱስ ቃላቶች መግለጫ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣው «ከላይ» ነው። በእርግጥም ልባቸው ለበጎ ሥራ ለሚራብና ለሚጠማ በጣም ይረዳል። አንድ ሰው ሲፀፀት፤ ከኃጢአት ሲርቅ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በልቡ እንዲያድር ሲለምን፤ በሙሉ ልቡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኙ መሆኑን ሲያምን፤ ለዚህ ሰው ጌታ ራሱንና የራሱንም ደስታና ሰላም በአማኙ ልብ ያሳድራል። እኔም ይህን ጸጋ በ1930 ዓ.ም. ተቀበልሁ። ከዚያንም ጊዜ ጀምሮ ይህንን ግሩም ግንኙነት ከጌታዬ ጋር አላቋርጥኩም። እርስዎም እስካሁን ጌታን አዳኝዎና ጌታዎ አድርገው ያልተቀበሉ ከሆነ አሁኑኑ ራስዎን ለእርሱ እንዲሰጡ በማቻኮል አሳስብዎታለሁ።

ዋትሰን ጉድማን



### የዮሐንስ ወንጌል 3፡

16፤ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።»

### 1ኛ ዮሐንስ 4፡

8፤ «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።»
9፤ «በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና።»

### ትንቢተ ኤርምያስ 31፡

3፤ «እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ፥ እንዲህም አለኝ፡— በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ።»

### የዮሐንስ ራእይ 1፡

5፤ «ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፥ ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።»

## 2 የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት።

የዮሐንስ ወንጌል 14፥

9፤ «ኢየሱስም አለው፦ አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ፦ አብን አሳየን ትላለህ?

10፤ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል።»

የማቴዎስ ወንጌል 1፥

22፤ «በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦

23፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።»

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥

16፤ «እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።»

## ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ 3

ትንቢተ ኢሳይያስ 9፥

6፤ «ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።»

የማቴዎስ ወንጌል 17፥

5፤ «እርሱም ገና ሲናገር፥ እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፥ እነሆም ከደመናው፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።»

የሉቃስ ወንጌል 1፥

35፤ «መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።»

1ኛ ዮሐንስ 4፥

15፤ «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፥ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።»

## 4 ኢየሱስ ማን እንደሆነ ይነግረናል

የዮሐንስ ወንጌል 10፥

7፤ «ኢየሱስም ደግሞ አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ።»

የዮሐንስ ወንጌል 8፥

23፤ «እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም።»

የዮሐንስ ወንጌል 8፥

58፤ «ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።»

የዮሐንስ ወንጌል 11፥

25፤ «ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።»

የዮሐንስ ወንጌል 6፥

35፤ «ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፥ በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።»

የዮሐንስ ወንጌል 9፥

5፤ «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።»

## ኢየሱስ ከፈጸማቸው ታምራቶች ጥቂቶቹ 5

የማቴዎስ ወንጌል 14፥

19፤ «ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፥ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።

20፤ ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ።

21፤ ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር።»

የሉቃስ ወንጌል 5፥

4፤ «ነገሩንም ከጨረሰ በኋላ፥ ስምዖንን፦ ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል፤ መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ አለው።

5፤ ስምዖንም መልሶ፦ አቤቱ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ አለው።

6፤ ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ።»

## 6 ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪና ጌታ ነው

**ቆላስይስ 1፡**

16፤ «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋልና።»

**የዮሐንስ ወንጌል 1፡**

3፤ «ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።»

**ሮሜ 14፡**

9፤ «ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።»

**ዕብራውያን 1፡**

2፤ «ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።»

**የሐዋርያት ሥራ 2፡**

36፤ «እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።»

## ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ዳኛ ነው 7

**የማቴዎስ ወንጌል 25፡**

32፤ «አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፥ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል።»

**የዮሐንስ ወንጌል 5፡**

22፤ ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም።

**ሮሜ 2፡**

16፤ «ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል።»

**የሐዋርያት ሥራ 10፡**

42፤ «ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደሆነ እንመሰክር ዘንድ አዘዘን።»

**ሮሜ 14፡**

10፤ «አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና።»

## 8 መዳን በክርስቶስ በኩል ብቻ

**ዕብራውያን 5፡**

9፤ «ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።»

**የዮሐንስ ወንጌል 14፡**

6፤ «ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።»

**የዮሐንስ ራእይ 5፡**

9፤ «መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ።»

**የዮሐንስ ወንጌል 8፡**

24፤ «እንግዲህ፦ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ እንደ ሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው።»

**የዮሐንስ ወንጌል 10፡**

9፤ «በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።»

**ቆላስይስ 1፡**

12፤ «በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገስ እንደ



ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።
13፤ እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥
14፤ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።»

**1ኛ ቆሮንቶስ 1፡**

30፤ «ነገር ግን፦ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።»

**የሐዋርያት ሥራ 4፡**

12፤ «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።»

**የሉቃስ ወንጌል 19፡**

10፤ «የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።»

**ቲቶ 2፡**

14፤ «መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።»

## 10 የክርስቶስ ደም አዳኝነት

1ኛ ዮሐንስ 1፥

7፤ «ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።»

ኤፌሶን 1፥

7፤ በውድ ልጁም፥ እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።

1ኛ ጴጥሮስ 1፥

18፤ 19፤ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።»

ዕብራውያን 9፥

14፤ «ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?»

## በክርስቶስ አምኖ መዳን 11

ኤፌሶን 2፥

8፤ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
9፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።»

ሮሜ 5፥

1፤ «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤»

1ኛ ዮሐንስ 5፥

4፤ «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።»

የዮሐንስ ወንጌል 20፥

31፤ «ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።»

የዮሐንስ ወንጌል 6፥

28፤ «እንግዲህ፦ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት።

29፤ ኢየሱስም መልሶ፦ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።»

## 12 የእግዚአብሔር ምሕረት

መዝሙር (103)፥

11፤ «ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ።»

መዝሙር (103)፥

17፤ «የእግዚአብሔር ምሕረት ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ፥ ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው።»

ሰቆቃወ ኤርምያስ 3፥

22፤ «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና።

23፤ ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው።»

ቲቶ 3፥

5፤ «እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፤»

መዝሙር (108)፥

4፤ «ምሕረትህ በሰማይ ላይ ታላቅ ናትና፥ እውነትህም እስከ ደመናት ድረስ ነውና።

## እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድንሔድ ያዛል 13

የማቴዎስ ወንጌል 11፥

28፤ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።»

የዮሐንስ ወንጌል 7፥

37፤ «ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፦ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።»

ትንቢተ ኢሳይያስ 1፥

18፤ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።»

የሉቃስ ወንጌል 14፥

17፤ «በእራትም ሰዓት የታደሙትን፦ አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲላቸው ባሪያውን ላከ።»

የዮሐንስ ራእይ 22፥

17፤ «መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።»

## 14 ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም

1ኛ ዮሐንስ 3፥
10፤ «የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።»

2ኛ ቆሮንቶስ 6፥
17፤ «ስለዚህም ጌታ፦ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኵስንም አትንኩ ይላል፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፦ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል።»

ሮሜ 8፥
14፤ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።
15፤ አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።»

## እግዚአብሔር ስለ ጠንካራ መጠጥ የተናገረው 15

ሮሜ 13፥
13፤ «በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤
14፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።»

ኢሳይያስ 5፥
11፤ «ስካርን ለመከተል በጥዋት ለሚማልዱ፥ የወይን ጠጅም እስኪያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸው!»

መጽሐፈ ምሳሌ 23፥
31፤ «ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት፥ በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ።
32፤ በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል።»

የሉቃስ ወንጌል 21፥
34፤ «ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።»

## 16 ቁም ነገረኛነት አይበቃም

የማቴዎስ ወንጌል 22፥
37፤ «ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።
38፤ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።»

ዕብራውያን 3፥
13፤ «ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤»

ምሳሌ 16፥
25፤ «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።»

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥
12፤ «ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለቈጠረኝ፥ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ፤
13፤ አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን፤ ይህን አደረገልኝ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ።»

## አትታለሉ 17

ያዕቆብ 1፥
22፤ «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።»

1ኛ ቆሮንቶስ 6፥
9፤ «ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ፥ ወይም ሌቦች
10፤ ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።»

ኤፌሶን 5፥
6፤ «ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ።»

1ኛ ዮሐንስ 3፥
7፤ «ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው።
8፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።»

## ኃጢአት ሞትን ያመጣል

**ሮሜ 5፡**

12፤ «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤»

**ያዕቆብ 1፡**

15፤ «ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።»

**ሮሜ 8፡**

6፤ «ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።»

**ሮሜ 6፡**

21፤ «እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና።»

**ምሳሌ 11፡**

19፤ «በጽድቅ የሚጸና በሕይወት ይኖራል፤ ክፋትን የሚከተል ግን ለሞቱ ነው።»

## ክርስቶስ ሞትን አሸነፈ



**የዮሐንስ ወንጌል 11፡**

43፤ ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ፡— አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ።

44፤ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበረ። ኢየሱስም፡— ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው።

**የዮሐንስ ራእይ 1፡**

18፤ ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።

**የዮሐንስ ወንጌል 10፡**

17፤ ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና፤ ስለዚህ አብ ይወደኛል።

18፤ እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።

**የሉቃስ ወንጌል 7፡**

14፤ ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም፡— አንተ ጐበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ።

15፤ የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት።



## አሥሩ ትእዛዛት

**ዘዳግም 5፡**

7፤ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።

8፤ በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፤

9፤ 10፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውም።

11፤ የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

12፤ እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ ጠብቅ።

13፤ ስድስት ቀን ሥራ ተግባራህንም ሁሉ አድርግ፥

14፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ እንደምታርፍ ሎሌህና ገረድህ ያርፉ ዘንድ፥ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም



ውስጥ ያለ እንግዳ፤ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ።

15፤ አንተም በግብፅ ባሪያ እንደ ነበርህ አስብ፤ እግዚአብሔር አምላክህ በጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ ከዚያ አወጣህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ።

16፤ እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝም፥ መልካምም እንዲሆንልህ።

17፤ አትግደል።

18፤ አታመንዝር።

19፤ አትስረቅ።

20፤ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።

21፤ የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ፤ የባልንጀራህንም ቤት እርሻውንም ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም፥ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።

**የዮሐንስ ወንጌል 13፡**

34፤ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

## 22 ከእግዚአብሔር መሸሸግ አይቻልም

መጽሐፈ ምሳሌ 15፡

3፤ የእግዚአብሔር ዓይኖች በስፍራ ሁሉ ናቸው፤ ክፉዎችንና ደጎችን ይመለከታሉ፤

መዝሙር (139)፡

8፤ ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ።

12፤ ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥ ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና፤ እንደ ጨለማዋ እንዲሁ ብርሃንዋ ነው።

መጽሐፈ ኢዮብ 34፡

21፤ ዓይኖቹ በሰው መንገድ ላይ ናቸው፥ እርምጃውንም ሁሉ ያያል።

22፤ ኃጢአትን የሚሠሩ ይሰወሩበት ዘንድ ጨለማ ወይም የሞት ጥላ የለም፤

ትንቢተ ኤርምያስ 23፡

24፤ ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር።

## የኃጢአተኞች የዘላለም ቅጣት 23

የማቴዎስ ወንጌል 13፡

41፤ የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥

42፤ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፤

መዝሙር 9፡

17፤ ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፥ እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ።

2ኛ ጴጥሮስ 3፡

7፤ አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።

የዮሐንስ ራእይ 20፡

15፤ በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።

የማቴዎስ ወንጌል 25፡

46፤ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።

## 24 የወደፊት ዳኝነት

2ኛ ጴጥሮስ 2፡

9፤ ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፥ በደለኞችንም ይልቁንም በርኵስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል።

የሐዋርያት ሥራ 17፡

31፤ ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል።

ሮሜ 14፡

12፤ እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።

ዕብራውያን 9፡

27፤ ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፤

1ኛ ዮሐንስ 4፡

17፤ በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ 25

ሮሜ 5፡

15፤ ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።

የሐዋርያት ሥራ 4፡

33፤ ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው።

2ኛ ቆሮንቶስ 9፡

15፤ ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን።

2ኛ ቆሮንቶስ 8፡

9፤ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።

ሮሜ 9፡

17፤ እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።

## ንስሐ

የሐዋርያት ሥራ 3፡

19፤ እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።

ሉቃስ 13፡

3፤ እላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ።

የሐዋርያት ሥራ 2፡

38፤ ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

ሉቃስ 15፡

7፤ እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።

የሐዋርያት ሥራ 17፡

30፤ እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል።

## የኃጢአት ይቅርታ



ትንቢተ ኢሳይያስ 55፡

7፤ ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ።

የሐዋርያት ሥራ 5፡

31፤ ይህን እግዚአብሔር፥ ለእስራኤል ንስሐን የኃጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ፥ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው።

የዮሐንስ ራእይ 3፡

20፤ እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።

የማቴዎስ ወንጌል 6፡

14፤ ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማይ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

ትንቢተ ሕዝቅኤል 18፡

21፤ ኃጢአተኛውም ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትእዛዜንም ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም።



## ከዓለማዊ ተግባር መለየት

1ኛ ዮሐንስ 2፡

15፤ 16፤ ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።

ትንቢተ ኢሳይያስ 1፡

16፤ ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፤ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፤ ክፉ ማድረግን ተዉ፥

ቆላስይስ 3፡

2፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።

ያዕቆብ 4፡

4፤ አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።

## አዲሱ ልደት



የዮሐንስ ወንጌል 3፡

3፤ ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።

2ኛ ቆሮንቶስ 5፡

17፤ ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

1ኛ ዮሐንስ 5፡

18፤ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን።

1ኛ ጴጥሮስ 1፡

23፤ ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።

1ኛ ዮሐንስ 2፡

29፤ ጻድቅ እንደሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ እወቁ።

## 30 በኃጢአት ሞት በክርስቶስ ትንሣኤ

### ኤፌሶን 2፡

1፤ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

7፤ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።

### ቆላስይስ 3፡

1፤ እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤

### 1ኛ ጴጥሮስ 2፡

24፤ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።

### ገላትያ 5፡

24፤ የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

## የዘለዓለም ሕይወት 31

### ሮሜ 6፡

23፤ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።

### የዮሐንስ ወንጌል 3፡

36፤ በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።

### ገላትያ 6፡

8፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።

### የዮሐንስ ወንጌል 5፡

24፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።

## 32 የመዳን ማረጋገጫ

### ገላትያ 4፡

6፤ ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።

### 1ኛ ዮሐንስ 3፡

18፤ ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።

19፤ ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ሁሉ፥ ከእውነት እንደ ሆንን በዚህ እናውቃለን በፊቱም ልባችንን እናሳርፋለን፥

### ሮሜ 8፡

16፤ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።

### የዮሐንስ ወንጌል 13፡

21፤ ኢየሱስ ይህን ብሎ በመንፈሱ ታወከ፤ መስክሮም፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ።

### 1ኛ ዮሐንስ 4፡

13፤ ከመንፈሱ ስለ ሰጠን፥ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን።

## ክርስቶስ በውስጣችን ሲያድር የሚሰጠን ደስታ 33

### የዮሐንስ ወንጌል 17፡

13፤ አሁንም ወደ አንተ እመጣለሁ፤ በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈጸመ እንዲሆንላቸው ይህን በዓለም እናገራለሁ።

### ሮሜ 14፡

17፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።

### መዝሙር (16)፡

11፤ የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፥ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።

### ገላትያ 2፡

20፤ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

## 34 ለጌታችን የመታዘዝ አስፈላጊነት

1ኛ ሳሙኤል 12፡

15፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ፥
በእግዚአብሔርም ትእዛዝ ላይ ብታምፁ፥
በእናንተና በንጉሣችሁ ላይ የእግዚአብሔር እጅ
ትሆናለች።

ሮሜ 6፡

16፤ ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን
ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት
ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም
ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ
የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።

2ኛ ተሰሎንቄ 1፡

6፤ 7፤ ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር
ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ፥ መከራን
ለሚያሳዩአችሁ መከራን፥ መከራንም
ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት
አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት
በእርግጥ ጽድቅ ነውና።

8፤ እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ ለጌታችንም
ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤

9፤ 10፤ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር፥
ምስክርነታችንንም አምናችኋልና በሚያምኑት
ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፥ ከጌታ ፊት
ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።

## ስለ ክርስቶስ የመመስከር አስፈላጊነት 35

1ኛ ዮሐንስ 2፡

23፤ ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ
የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ
አለው።

ማቴዎስ 10፡

32፤ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ
እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት
እመሰክርለታለሁ፤

33፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ
ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት
እክደዋለሁ።

ሮሜ 10፡

9፤ ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ
ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን
እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤

10፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም
መስክሮ ይድናልና።

ፊልጵስዩስ 2፡

11፤ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር
ዘንድ ነው።

## 36 ሰይጣን ተቀዳሚ ጠላታችን

የማቴዎስ ወንጌል 4፡

1፤ ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን
ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው።
10፤ ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ አንተ ሰይጣን
ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ
አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው።
11፤ ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው፥ እነሆም
መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 26፡

18፤ የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን
በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥
ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን
ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን
ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ
ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡

9፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር
ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት
በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች
ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ
ሰይጣን አሠራር ነው።

ኤፌሶን 6፡

11፤ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ
እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ
ልበሱ።

## በሰይጣን ላይ ድል 37

ያዕቆብ 4፡

7፤ እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤
ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤

8፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም
ይቀርባል።

ዕብራውያን 2፡

14፤ 15፤ እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም
ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ
ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም
ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ
ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ
ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ
ተካፈለ።

1ኛ ዮሐንስ 3፡

8፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥
ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።
ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ
የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡

8፤ በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ
የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው
ዓመፀኛ ይገለጣል፤

### 1ኛ ዮሐንስ 4፡

20፤ ማንም፡- እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?

### ገላትያ 5፡

22፤ የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥

23፤ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።

### የዮሐንስ ወንጌል 13፡

35፤ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።

### 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡

1፤ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።



### የሐዋርያት ሥራ 10፡

39፤ እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን፤ እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት።

40፤ እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤

41፤ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን።

### የዮሐንስ ወንጌል 20፡

26፤ ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።

27፤ ከዚያም በኋላ ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።

28፤ ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት።



### ሮሜ 6፡

3፤ ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?

4፤ እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

5፤ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን።

### የዮሐንስ ወንጌል 5፡

25፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰአት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።

28፤ 29፤ በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።



### 2ኛ ቆሮንቶስ 7፡

1፤ እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፥ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን፥ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።

### 1ኛ ጴጥሮስ 1፡

15፤ ዳሩ ግን፡- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።

### ዕብራውያን 13፡

12፤ ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።

### 1ኛ ዮሐንስ 1፡

9፤ በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።

### ኤፌሶን 1፡

4፤ ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።

ሮሜ 8፡

9፤ እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ
በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ
አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው
ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።

የሐዋርያት ሥራ 13፡

52፤ በደቀ መዛሙርትም ደስታና መንፈስ
ቅዱስ ሞላባቸው።

ትንቢተ ሕዝቅኤል 37፡

27፤ ማደሪያዬም በላያቸው ላይ ይሆናል፤
እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ
ይሆኑኛል።

የሐዋርያት ሥራ 1፡

8፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ
በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥
በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም
እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ
ትሆናላችሁ አለ።

የሐዋርያት ሥራ 4፡

31፤ ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት
ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ
ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ
ተናገሩ።



መዝሙር (34)፡

18፤ እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ
ነው፥ መንፈሳቸው የተሰበረውንም
ያድናቸዋል።

የማቴዎስ ወንጌል 6፡

33፤ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ
ይጨመርላችኋል።

መዝሙር 37፡

3፤ በእግዚአብሔር ታመን፥ መልካምንም
አድርግ፥ በምድርም ተቀመጥ፥ ታምነህም
ተሰማራ።
4፤ በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም
መሻት ይሰጥሃል።

1ኛ ጴጥሮስ 4፡

12፤ ወዳጆች ሆይ፥ በእናንተ መካከል እንደ
እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ
ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ።

13፤ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት
እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ
መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ።



ዕብራውያን 2፡

18፤ እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ
የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

ሮሜ 16፡

20፤ የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ
በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

መዝሙር (34)፡

19፤ የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፥
እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል።

ሮሜ 8፡

28፤ እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ
አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ
እናውቃለን።

1ኛ ቆሮንቶስ 10፡

13፤ ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም
ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን
ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ
የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥
ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር
መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።



የዮሐንስ ራእይ 3፡

5፤ ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ
ይጎናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ
አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት
ለስሙ እመሰክርለታለሁ።

የዮሐንስ ራእይ 21፡

7፤ ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም
እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።

የዮሐንስ ራእይ 2፡

7፤ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን
ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው
በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ
እንዲበላ እሰጠዋለሁ።

የዮሐንስ ራእይ 3፡

21፤ እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴም
ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ፥ ድል
ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ
እሰጠዋለሁ።

## 46 እግዚአብሔር ስለ መፋታት ይነግረናል

### የሉቃስ ወንጌል 16፡

18፤ ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፥ ከባልዋም የተፈታችውን የሚያገባ ያመነዝራል።

### ሮሜ 7፡

2፤ ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች።

3፤ ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።

### የማቴዎስ ወንጌል 5፡

32፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

## የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት 47

### የማቴዎስ ወንጌል 24፡

27፤ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤

### የማቴዎስ ወንጌል 24፡

30፤ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል።

### 1ኛ ዮሐንስ 3፡

2፤ ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።

### የዮሐንስ ወንጌል 14፡

3፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።

### የሉቃስ ወንጌል 12፡

40፤ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

## 48 የሉቃስ ወንጌል 21፡

27፤ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል።

### የማቴዎስ ወንጌል 16፡

27፤ የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።

### የዮሐንስ ራእይ 16፡

15፤ እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።

### የሐዋርያት ሥራ 1፡

11፤ ደግሞም፡— የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።

## የእግዚአብሔር ቃል

### 2ኛ ጴጥሮስ 1፡

21፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።

### መዝሙር (119)፡

11፤ አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።

### 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡

16፤17፤ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

### መዝሙር (119)፡

105፤ ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።

### የማቴዎስ ወንጌል 22፡

29፤ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡— መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።

Published in numerous languages by World Missionary Press as God supplies funds in answer to prayer. If you would like more copies for careful distribution, please write in English to:

**World Missionary Press, Inc.**
**P.O. Box 120**
**New Paris, IN 46553-0120 USA**

www.wmpress.org

Amharic HFA